# ለምን ተፈጠርኩኝ?

እስኪ ሁላችሁም አስቡ፣ ገምግሙ፣

ምን ይመስላችኋል የኑሮ ትርጉሙ።

የመኖርን ትርጉም ምስጢሩን እወቁ፣

ለምን ተፈጠርኩኝ ብላችሁ ጠይቁ።

ለምን ተፈጠርኩኝ?

ለሙብላት ለማውራት፣

ለማፍረስ ለመሥራት፣

ለመውረድ ለመውጣት፣

ተኝቶ ለመንቃት፣

ዳግም ለመተኛት፣

ሲመሽ  ለመጋደም፣

ሲነጋ ለሙብላት ከባቢን ለማውደም፣

ለምን ተፈጠርኩኝ?

መድሃኒት በመሥራት፣

ሕመምን ለማጥፋት፣

እርሃብ ለማስገድ አምርቶ ለማብላት

ወይስ ለመግደል ነው?

ዘሩን ለመጨረስ

መሰል የሰውን ልጅ በጭካኔ መንፈስ?

ወይስ  ለመፈወስ፣

ተፈጥሮን ለውጦ ከባቢን ለማደስ፣

ወይንስ ተፈጥሮን ለማውደም ለማፍረስ?

ቁም ነገር ሳይሠሩ ለመተረማመስ፣

ወይስ እንዳሸዋ መሬትን ለማልበስ።

ለምን ተፈጠርኩኝ?

ተዋልዶ ለሙብዛት፣ሞቶ ለመቀነስ፣

ወደነበሩበት አፈር ለመመለስ፣

ትቢያ አቧራ ሆኖ ለመድቀቅ ለመፍረስ?

ለምን ተፈጠርኩኝ?

ለመጥቀም ለመጉዳት፣

ለማጥፋት ለማልማት

ለማዳን ለመግደል

ሰውን ለመበደል፣

ለመውደድ ለመጥላት፣

ወይስ ለመቀማት፣

ሳይሰሩ ለመብላት፣

ስልጣን ተገን አርጎ ሙብትን ለመግፈፍ፣

እየደበደቡ በጥይት በሰደፍ፣

አገር ለመበዝበዝ ዘርፎ ለማዘረፍ።

ወይስ ለቁጥር ነው በዝቶ ለመባዛት

ቁም ነገር ሳይሰሩ መሬትን ለመሙላት።

እንደ ሰው ተፈጥሮ እንዳራዊት ማሰብ፣

መሻማት መስገብገብ፣

ማግበስበስ መሰብሰብ፣

ለምን ተፈጠርኩኝ?

ድህነት ለማጥፋት

ወይስ ለማስፋፋት

እንደሰው ተፈጥሮ እንዳሳማ መብላት፣

እንደ ሰው ተወልዶ እንደ ትንኝ መሞት፣

ከሆነ ትርጉሙ እዚህ ዓለም መምጣት

አያድርስ ቅጣት ነው ከቅጣትም ቅጣት።

ለምን ተፈጠርኩኝ?

እንክት ድቅቅ አርጎ ከባቢን ለማፍረስ፣

ወይስ ለማሻሻል በወጉ ለማደስ?

የተፈጥሮን ጸጋ በጉልበት ለመዝረፍ?

ወይስ ለማድረግ ነው ለሁሉም እንዲተርፍ?

ወይስ ለመስራት ነው ውል ያለው ቁም ነገር፣

ችሎታን ተጠቅሞ ኑሮን ለመቀየር፣

በረዶ በማቅለጥ፣በረሃ በማልማት

ለሕይወት እንዲስማማ አድርጎ ለመስራት።

ህመሙን በጤና፣መጥፎውን በመልካም፣

እራቡን በጥጋብ፣ግጭቱን በሰላም።

ጥላቻን በፍቅር፣

ተክቶ ለመኖር፣

ወይስ በዘር በእምነት ፣

እርስ በርስ ለመባላት፣

ያለውን አፍርሶ ባዶ እጁን ለመቅረት።

በሰላም በጸጋ ተባብሮ ከመኖር፣

ከድህነት ወድቆ ለምኖ ለማደር፣

ወይስ ለመሆን ነው ከአፈር ወደ አፈር፣

ምን ይሆን ንገሩኝ የመኖርን ምስጢር።

አገሬ አዲስ

2009 ዓ.ም.እ.አ.